ጎሕ

# የጎንደር ሕብረት

gonderhibrert72@gmail.com /website: www.gonderhibret.org

## ይድረስ ለተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች!

በአገራችን ላይ እያንዣበበ ያለው ጥቁር ደመና እና በመሬት ላይ የሚታየው ገደል ጎንደር ህብረትን እጅግ አሳስቦታል። ስለዚህ ኡ! ኡ ታውን ለፖለቲካ ድርጅቶች ለማቅረብ ተገዷል።

ኢትዮጵያ አገራችን ከዚህ ቀደም ከሳለፈቻቸው አስከፊ ክስተቶች በበለጠ አደጋ ላይ የወደቀችበት ዘመን ቢኖር የአሁኑ እጅግ የከፋ ነው ብንል ማጋነን አይሆንም።

አው! በርግጥ ቀደም ባለው ታሪኳ ብዙ ችግሮችን ያለፈች አገር መሆኗ ይታወቃል። ዛሬ እያመሳት ያለው ችግር ግን በብዙ መልኩ ከዚህ ቀደም ታይቶ የማይታወቅ ነው ስንል በርግጠኛ ነት ነው። ከዚህ በፊት ከባድ የሚባሉ የኢኦኖኖም ቀውሶች፤ በሰው ሰራሺና በተፈጥሮ ርሃብ እና በተደጋጋሚ የተሰነዘረባት የውጭ ወርራ ነበር። ከውጭ ወራሪ ጋር ከፍተኛ የሆኑ ጦርነቶች በአድዋ፤ በማይጨው ከጣሊያን ወራሪ ጋር፤ በምዕራብ ከድርቡሾች ጋር፤ በምሥራቅ ክግብፆች፤ በስሜን ከግብጾሽና ከቱርኮች ጋር፤ እንደገና በምሥራቅ ከሱማሊ ወራሪዎች ጋር ፤ ጦርነት ተደርጓል። ብዙ የሰው ሂይዎትና ንብረት፤ የኃይማኖት ማምለኪያ ቦታዎችና ቅርሶች ወድመዋል። ብርቅየ የሆኑ ለአገራቸው ቀናይዕ የነበሩ አገር ወዳድ አያት ቅድም አያቶቻችንን ለአገራቸው ክብር ውድ ህይዎታቸውን ገብረዋል። ዛሬ በኩራት የነፃነት ታሪካችንን እየዘከርን የምንኖረው እኒያ አባቶቻችን በከፈሉልን የህይዎት ዋጋ ነው።

በደርግ ፋሺስታዊ መንግሥት ጊዜም ቢሆን በጣም በተራዘመ ጦርነትና እርሃብ ብዙ ወገኖቻችንን አጥተናል። ለሐገርና ለወገን አለኝታ ይሆናሉ የተባሉ መተኪያ የሌላቸው ብርቅየ የአገሪቱ ምሁራን ተረሽነዋል። ወላጆች የልጆቻቸውን ሬሳ በራቸው ላይ ፊት ለፊት እያዩ አልቅሰው ለመቅበር የተከለከሉበትን የልብ ሥብራት መከራ ሁሉ አሳልፈናል። ከዚያ አሰቃቂ ዘመን በህይዎት በተረፉት ሁሉ ላይ የአዕምሮ ጠባሳው እስካሁን ድረስ አብሯቸው ይኖራል። ክፉ ክፉውን ካስብን ብዙ ችግሮችን ሕዝባችን አሳልፉል። አገራችን አልቅሳለች።

ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ሕዝባችን በጎሳ ተከፋፍሎ እርስ በርሱ ወደ መጠፋፋት አልገባም። ጠላትን ለመመከትና የአገራችን ዳር ድንበር ለማስከበር ዘር ሳይለየው በአንድ ምሽግ ውስጥ አብሮ ደሙን አፍሥሷል ፤ አጥንቱን ከስከሷል። ጠላቱን ዶግ አመድ አድርጓል። ለዚህ ደግሞ እነ ባልቻ አባ ነብሶ እና እነ ራስ መኮንን፤ እነ እራስ አሉላ እና እነ ንጉሥ ሚካኤል በአንድ የጦር ግንባር ዘመተው ጠላትን መከተዋል። ሁሉም ዘር ሳይለያቸው ጭብጥ በሶ ተካፍለው እየበሉ በአንድ ኮዳ ውሃ እየተቀባበሉ በመጎንጨት ጠላትን መክተዋል። ኮርተው አገራቸውን አኩርተዋል።

ዛሬ ግን አይበለው እንጅ የውጭ ጠላት ቢመጣብን የመጣውን ጠላት ትተን እርስ በእርሳችን ለመዋጋት ተመቻችተናል። እንኳን ደንበር ጥሶ የመጣንውን የውጭ ጠላት አገር በቀል የሆነውን የወያኔን ዘረኛ መንግሥት በአንድ ላይ ቁመን ለመዋጋት ያልቻልን ደካማዎችና እራስ ወዳዶች ሆንን መገኘታችን በታሪክ የሚያስጠይቅ እንደሆነ

እያንዳንዳችን እናውቀዋለን። በአደባባይ ቆመንም ሆነ የብዙሃንን መገናኛዎችን ተጠቅመን ለሕዝብ የምንነግረው

የፖለትካ መርኋችን ተመሳሳይ፤ የምንናገረው ቋንቋ ግልጽ በሀገር ጉዳይ ላይ ያነጣጠረ ሆኖ ሳል ለምን ብቻ ለብቻ ለመታገል እንደምንፈልግ ሊገባን አልቻለም። አገራችን ከገደል ጠርዝ ላይ ነች። ወያኔ ወደ ማትመለስበት መቀመቅ ከከታት በታሪክ ተጠያቂው ገፍቶ ገደል የከተታት ወያኔ ብቻ ሳይሆን እኛ ቁመን እያየን ተባበርን ልናድናት ያልቻልነው ልጆቿ ሁሉ እኩል ተጠያቂዎች ነን። ታዲያ እስከመቸ ነው ተነጣጥለን ቁመን የምናዬው?

አዎ! በጥቂቱም ቢሆን ከዚህም ከዚያም ቁጭ ቁጭ ያሉ የመተባበር ጅምሮችን በአገር ቤትም ሆነ በውጭ አገር እያየን ነው። ነገር ግን አካሂዳቸውና የጥምረት ገመዳቸውን ስናይ አሁን አገሪቱ ላለችበት ሁኔታ ሊደርስ አለመቻሉን ስናይ ቁጭት ውስጣችን እየበላው ተስፋችን ደብዛዛ እንዲሆን እያደረገው ነው። ከአራት ዓመት በላይ የሆነው ሸንጎ ሲመሰረት በጣም ጥሩ ተስፋ ጥለን ነበር ሆኖም ግን በዚያ ስብስብ ውስጥ ሌሎችም ባለመጠቃለላቸው ሁሉን ነገር ጎደሎ አስመስሎታ። ተስፋችንም አደብዝዞታል። አሁን በአለፈው አመት ደግሞ ጥምረት ሲመሰረት በነበርው እንቅስቃሴ ሸንጎንም ጠቅልሎ ይወጣል ብለን ተስፋ ስናደርግ የተወሰኑ ድርጅቶች ብቻ ተጣምረው ሌሎች ሲቀሩ ሌላው አሳዛኝ ክስተት ሆኗል። አገርቤት ያሉ ተቃዋሚ ድርጅቶችም ከዚህ ከውጭ ያሉት እንደሚያደርጉት ሁሉ በአንድ ወቅት ተስፋ ሰጭ ነገር ሲያሳዩን በሌላ ጊዜ ደግሞ ተመልሰው ወደነበሩበት ነጠላ ክብር ይመለሳሉ። ታዲያ ምን ማለት እንችላለን? ይህ ሆድን ባር ባር አያስኝም?

ይሁን እንጂ አሁንም ተሥፋን ሰንቆ ለትግሉ የሚያስፈልግገውን መስዋዕትነት ከመክፈል አንዘናጋም። በመሆኑም፤ በቅርቡ በሲያትል ከተማ በሲቪክ ድርጅቶች አማካኝነት የተደረገው የፖለቲካ ድርጅቶች ውይይት እጅግ ተስፋ ሰጭ ሆኖ አግኝተናዋል። ምክንያቱ ከአገርቤትና ከውጭ ያሉ ዋና ዋን የተባሉ የፖለቲካ ተዋናኞች የተካፈሉበትና ላላ ያለም ቢሆን የጋራ ኮሚቴ አቁቁመው ተለያይተዋል። ይህ የተቁቋመው የጋራ ኮሚቴ አፋጣኝ ሥራ ሰርቶ ከሁኔታዎች ጋር እራሱን አጠናክሮ ሕዝባችን ለመምራት ያለውን ብቃት ካላሳየ የአገራችን ሁኔታ ወደት ተባባሰ ወታደራዊ አገዛዝ እየገባች መሆኑን በእርግጠኝነት ልንገነዘብ ይገባል። ይህ የተቋቋመው የጋራ ኮሚቴ ወደ ተግባራዊ ሥራ እንዲሰማራ ከፈለግን ደግሞ እያንዳንዱ በጉዳዮ የሚያገባቸው ድርጅቶች ሁሉ ያልጠቆጠበ ድጋፍ ሊያደርጉለት ይገባል።

ወያኔ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጇል። ተለጣፊው ፓርላማም ህጋዊ የግደያ ፈቃድ መስጠቱን ሰምተናል። ታዲያ ይህ የአስቸኳይ ጊዜ ዋጅ አገሪቱን ወደየት የሚወስዳት ይመስላችኋል? ይህን ጥያቄ ከናንተ በበለጠ እኛ መልሱን አናውቀውም።

የጎንደር ህብረት ለኢትዮጵያ አንድነት በአገራችን ሰማይ ላይ እያንዣበበ ያለውን ጥቁር ደመና አስቀድሞ ስለተረዳ እናንተን የፖለቲካ ድርጅቶች ተማጽኖ ለማቅረብ ተገዷል። ከላይ እንደ ጠቀስነው በተቃዋሚ የፖለቲካ መድረክ የተሰልፍን ሁሉ ለዚች አገር በጋራ ቁመን መፍትሄ ለማምጣት ሳንውል እና ሳናድር ዛሬውኑ እጅ ለእጅ ተያይዘን መራመድ ካልጀመርን ከታሪክ ተጠያቂነት አንድንም። ምንም ያህል ድርጅቴ ጠንካራ ነው ብንል እንደ ኢትዮጵያ ያልን ውስብሰብ የሆነ የፖለቲካ ሁኔታ ብቻችን ታግለን ወያኔን መጣልና አገር መመራት ፈጽሞ አንችልም። ይህን ደግሞ ሁላችሁም በመድረክ ላይ ብዙ ጊዜ ነግራችሁናል።

# የጎንደር ሕብረት

gonderhibrert72@gmail.com /website: www.gonderhibret.org

በእርግጥ ወያኔ ውስጡ የተቦርቦር እንጨት መሆኑ ይታወቃል፤ ሚገፋው ሲያጣ ነገ በራሱ ንኩትኩት ብሎ ሊወድቅ ይችላል። ታዲያ ያች አገር ምንድነው ምትሆነው? የፖለቲካ ፕሮግራማችሁ እንኳ ብዙም ልዩነት የሌላችሁ፤ ሁላችሁም ላንች ነው ሃገሬ ብላችሁ እየዘመራችሁ፤ ነገር ግን በጋራ ፕሮግራም ተባብራችሁ ~~ተሬ~~ መቆም ያቃታችሁ ይችን አገር እንዴት ነው የመምራት ሐላፊነቱን ልትወስዱ የምትችሉት?

እኛ በጎንደር ህብረድ ለኢትዮጵያ ድንድነት የምንታገል ውገኖቻችሁ መጭውን ሁኔታ ስናስበው በጣም ይጨንቀናል፤ ያመናል። ሁላችሁም እንደምትታመሙበት እናውቃለን ነገር ግን መዳህኒቱን በጉያችሁ ይዛችሁ መቀመጥ ህመሙን አይፈውስም።

በእኛ እምነት ያላችሁን ጥቃቅን የፖለቲካ ልዩነታችሁን ወደ ጎን በመተው ይበልጥ የሚያቀራርባችሁን አጠንክራችሁ በጋራ እንድትሰሩ በአገራንና ያለ መሪ የፖለቲካ ድርጅት እየተዋደቀ ባለው ህዝባችን ስም እንማጸናችኋለን።

ጎንደር ህብረት ለኢትዮጵያ አንድነት

አንድነት ኃይል ነው!

ኢትዮጵያ በተባበሩ ልጆቿ ነጻ ትወጣለች!

03/03/18